በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ትምህርት (እንደ ሁለተኛ ቋንቋ) የማጠቃለያ ፈተና ቢጋር

ህዳር/2017 ዓ.ም

መግቢያ

ይህ ሰነድ አራት ዋና ዋና የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የማጠቃለያ ፈተና ቢ.ጋርን ያካተተ ሲሆን የፈተና ይዘት ቢ.ጋር፣ የክህሎት ደረጃ ቴስት ቢ.ጋር እና የጥያቄ አይነቶች ቢ.ጋር ናቸው፡፡ የቢ.ጋሩ ዋና መሰረት የትምህርት ይዘቶችና ለይዘቶች የተሰጣቸው የክፍለ ጊዜ ድልድል ናቸው፡፡ የፈተና ይዘት ቢ.ጋር ለፈተናው የተመረጡት ይዘቶችና ከእያንዳንዱ ይዘት የተውጣጣውን የጥያቄ ብዛት ይዟል፡፡ እንዲሁም የጥያቄ አይነቶች ቢ.ጋር እያንዳንዱ ይዘት በየትኛው የፈተና አይነት እንደሚካተት ቀርቦበታል፡፡

የጥያቄዎቹ ብዛት መሰረት የሚያደርገውም ለትምህርቱ የተሰጠውን የክፍለ ጊዜ ብዛት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለይዘቱ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት ሲባዛ ጠቅላላ የጥያቄ ብዛት ሲካፈል ጠቅላላ የክፍለ ጊዜ ብዛት በሚል ቀመር ተሰልቶ ተዘጋጅቷል፡፡ ስለሆነም መምህራን ይህንን የቴስት ቢ.ጋር ተከትለው ፈተናዎችን ቢያዘጋጁ ወጥ አሰራር እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ቢ.ጋሩ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃና የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ብቃት (minimum learning competency) መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህንን ተከትሎም ፈተናው በሁለት መንፈቀ ዓመት ተከፍሎ ቀርቧል፡፡ ሁለቱ መንፈቀ ዓመታት እያንዳንዳቸው 20 ጥያቄዎችን የሚያካትቱ ሲሆን በድምሩ 40 ጥያቄዎችን አካትተዋል፡፡ ከጥያቄዎች አይነት አንጻር ደግሞ 5 ጥያቄዎች እውነት/ሐሰት፣ 3 ማዛመድ እና 12 የምርጫ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ከተማሪዎች ክሕሎት አንጻር ደግሞ አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች መካከለኛ ክብደት ያላቸው ሲሆን ቀላል እና ከባድ ጥያቄዎች ደግሞ የተመጣጠኑ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት መካከለኛ ክብደት ያላቸው ጥያቄዎች (ግንዛቤን፣ መረዳትንና ትግበራን የሚጠይቁ) 10 (50%)፣ ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ጥያቄዎች (ማስታወስን የሚጠይቁ) 5 (25%)፣ እንዲሁም ከፍተኛ ክብደት ያላቸው ጥያቄዎች (ማሰላሰልን፣ ማደራጀትን፣ መተንተንንና መገምገምን የሚጠይቁ) 5 (25%) ናቸው፡፡

የማጠቃለያ ፈተና ጥያቄዎች ቢጋር

የትምህርት አይነት፡- አማርኛ (እንደ ሁለተኛ ቋንቋ)

የትምህርት ዘመን፡- 2017ዓ.ም

የክፍል ደረጃ፡- 4ኛ ክፍል

የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 58

የአንደኛው መንፈቅ ዓመት

የምዕራፍ ቁጥር	ይዘት	ክ/ጊዜ	የትምህርት ባህርይ መለኪያዎች				ድምር	ፐርሰንት
			እውቀት	መረዳት	ትግበራ	ማጀራጀት መተንተን መገምገም		
1	ባህላዊ ልብሶች	14	3	1	1	-	5	20%
1.1	ማዳመጥና መናገር	4	(1ም)				1	
1.2	ማንበብና መፃፍ	6	(1ም)	(1ም) (ለ)	-	-	2	
1.3	ቃላት	1	1(አ)				1	
1.4	ሰዋስው	3			(1እ/ሀ)		1	
2	ቤተሰብ	14	3	2			5	25%
2.1	ማዳመጥና መናገር	4	(1ም)				1	
2.2	ማንበብና መፃፍ	6	(1እ/ሀ) (1ም)				2	
2.3	ቃላት	2		(1እ/ሀ)			1	
2.4	ሰዋስው	2		(ም)			1	
3	የውሃ አካላት	11	1	2	-	-	3	15%

3.1	ማዳመጥና መናገር	3	(1ም)	-	-	-	1	
3.2	ማንበብና መፃፍ	5		(1ም)	-	-	1	
3.3	ቃላት	3	-	(1ም)	-	-	1	
4	ተላላፊ በሽታዎች	10	2	1	1	-	4	20%
4.2	መናገር	2	(1እ/ሀ)	-	-	-	1	
4.3	ማነበብ	3	(1ም)	-	-	-	1	
4.4	መፃፍ	3	-	(1እ/ሀ)	-	-	1	
4.5	ሰዋሰው	2	-	-	(1ም)	-	1	
5	ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች	9	2	-	1	-	3	20%
5.3	ማንበብ	5	(2 አዛ)	-	-	-	2	
5.4	መፃፍ	4			(1ም)	-	1	
ድምር		58	11	6	3		20	100%

ቁልፍ ቃላት፡- እ/ሀ- እውነት /ሀሰት 5 አ- አዛምድ 3 ም- ምርጫ 12